# አሲምባ ውይይት መድረክ

2009 የዓመቱ መጨረሻ የትግላችን ግምገማ

የፈረንጆቹ ዓመት 2009 ወጥቶ እነሆ ዓዲሱ 2010 ዓመት ትላንትና ሲገባ አሲምባዎች በኢትዮጵያ ሀገራችን እየተደረገ ያለው የዴሞክራሲያዊ ትግል ከምን ላይ ደርሷል? ወደፊትስ አቅጫው ወዴት ቢሆን ጥሩ ነው የሚለውን ከነገው ቀዳሜ ጀምረን አንኳር አንኳር የሆኑ ባለፈው ዓመት የታዘብናቸውን ነጥቦች (ደካማም ሆነ ጠንካራ የትግሉን ጎኖች) በማንሳት በጥንቃቄ እንመረምራለን።

ባለፈው ዓመት በርካታ ለኢትዮጵያ ሕዝብ እየታገልን ነው የሚሉን ወገኖቸ በቀዳሚነት በተለያየ አቅጣጫ የዚያን ትውልድ ታሪክ የማብጠልጠሉ አባዜ በወያኔ ቡራኬ ባለፈው የደርግ ሥርዓት የማዕከላዊ ገራፊ ሻምበል የጻፈው ውሸት የሞላበት መጽሐፍ ጀምረን በቅርቡ ትግሉን ለወጣቱ ወገን ማስረከብ አለብን ብለው ትግል ያቆሙት ዶ/ር አብራ ስትታገል የነበረችውን የድርጅታቸውን መሪ እሥር ተወርውራ ባለችበት ወቅት ለችግሩ ሁሉ ተጠያቂ ለማድረግ ያፋቸው ማሟሟሻ ያደረጉት ያንኑ የፈረደበትን ትውልድ መሆኑን ስንሰማ በማዘን አድምጠን ያለፍንበት ዓመት ነው።  ሌላም ሌላ። በዚህ ወቅት ነው እንግዲህ አቶ ዓሊ ሁሴን "የትውልዱ ትውስታዎች - የዓሊ ሁሴን ሳኢድና የሌሎች ኢትዮጵያውያን የፖለቲካ ጉዳተኞች ታሪክ" የሚለውን ዶኩመንታሪ ባለፈው ዓመት በዓለም ዙሪያ ተበትነው ለሚገኙ ወገኖችና ለዓለም አቀፍ ሕብረተሰብ ያቀረቡት። በዚህም ጉዞአቸው የገጠሟቸውን ጥያቄዎቸን አስተያየቶች ሊያወያዩን ከመካከላችን ይገኛሉ።

የአሲምባ ውይይት መድረክ በሀገራችን ውስጥ እየተካሄደ ያለውን የዴሞክራሲያዊ የሕዝቡን ትግል አስመልክቶ የተለያዩ በሳል ሀሳቦች የሚንሸራሸርበት ነጻ የውይይት መድረክ ነው። ውስጥ እየተካሄደ ያለውን የዴሞክራሲያዊ ትግል አስመልክቶ የተለያዩ በሳል ሀሳቦች የሚንሸራሸርበት ነጻ የውይይት መድረክ ነው።